# Chapter 1

## CD 1

### Activity 1a

ፍጹም፡ ታድያስ!

ኤሊዛ፡ ታድያስ!

ፍጹም፡ ሰላም ነው?

ኤሊዛ፡ ሰላም ነው።

ፍጹም፡ ስምሽ ማን ይባላል?

ኤሊዛ፡ ስሜ ኤሊዛ ነው።
አንተስ፤ ስምህ ማን ይባላል?

ፍጹም፡ ስሜ ፍጹም ይባላል።

ኤሊዛ፡ ፍሱም?

ፍጹም፡ አይ, ፍጹም። ስሜ ፍጹም ይባላል።

ኤሊዛ፡ ፍሱም!

ፍጹም፡ አይ፤ ፍጹም.

ኤሊዛ፡ ፍሱም!

## CD 2

### Activity 2a

ኤሊዛ፡ ስምህ ማን ይባላል?

ፍጹም፡ ስሜ ፍጹም ይባላል።

ኤሊዛ፡ ስምህ ፍጹም ነው?

ፍጹም፡ አዎ፤ ስሜ ፍጹም ነው። አንቺስ፤ ስምሽ ማን
ነው?

ኤሊዛ፡ ስሜ ኤሊዛ ነው።

## CD 3

### Activity 2b

ቀ ፤ ጨ ፤ ጠ ፤ ፀ ፤ ጸ

## CD 4

### Activity 2c

ግርማ፡ ሰላም! ዳዊት ግርማ እባላለሁ።

ማርታ፡ ይቅርታ ማን አልከኝ?

ግርማ፡ ዳዊት ግርማ።

ማርታ፡ እሺ። አመሰግናለሁ።

ግርማ፡ አንቺስ፤ ማን ትባያለሽ?

ማርታ፡ ስሜ ማርታ ደስታ ይባላል።

ግርማ፡ ይቅርታ ማን አልሽኝ?

ማርታ፡ ማርታ ደስታ።

ግርማ፡ እሺ። አመሰግናለሁ። ታድያስ! ሰላም ነው?
ስምህ ማን ነው?

## CD 5

### Activity 3a

ኤሊዛ፡ እሺ፤ፍጹም።

ፍጹም። አቤት፤ ኤሊዛ!

ኤሊዛ፡ እንደምን ነህ?

ፍጹም። በጣም ደህና ነኝ። አንቺስ፤ ኤሊዛ, እንዴት ነሽ?

ኤሊዛ፡ ደህና ነኝ። እግዜር ይመስገን።

## 6

### Activity 4a

አስተናጋጅ፡ ሰላም ናችሁ?

ፍጹም፡ ሰላም ነው?

አስተናጋጅ፡ የሚጠጣ ምን ልታዘዝ?

ፍጹም፡ ለኔ አንድ ቡና እና አንድ ሊትር ውሃ።

አስተናጋጅ፡ ቀዝቃዛ ወይስ ከውጪ?

ፍጹም፡ ቀዝቃዛ

አስተናጋጅ፡ እሺ ሌላስ?

ኤሊዛ፡ ለኔ ደግሞ አንድ ቆላ!

አስተናጋጅ፡ ይቅርታ ምን?

ፍጹም፡ ሃሃሃ አንድ ኮካ ኮላ።

አስተናጋጅ፡ ኧ ነው እንዴ። እሺ። ቀዝቃዛ ወይስ ከውጪ?

ኤሊዛ፡ ቀዝቃዛ።

አስተናጋጅ፡ ሌላስ?

ፍጹም፡ በቃ።

ፍጹም፡ እሺ ኤሊዛ፤ እንዴት ነሽ?

ኤሊዛ፡ በጣም ደህና ነኝ። እግዜር ይመሰገን። አንተስ፤
እንደምን ነህ?

ፍፁም፡ እኔም በጣም ደህና ነኝ። ኤሊዛ የመጣሽው
ከምን ሀገር ነው?

ኤሊዛ፡ እኔ የመጣሁት ከጀርመን ሀገር ነው።አንተስ፤
የመጣኸው ከምን ሃገር ነው?

ፍጹም፡ እኔ የመጣሁት ከኢትዮጵያ ነው።

**dagi enters the cafe**

ዳጊ! ሄይ ፍጹም! ፍጹም፤ ደህና አደርክ?

ፍጹም፡ ደህና እግዜር ይመስገን። እንደምን አደርክ ዳጊ?

ዳጊ፡ እንዴት ነህ?

ፍጹም፡ ደህና ነኝ። አንተስ? ደህና ነህ?

ዳጊ፡ እኔም ደህና ነኝ።

ፍጹም፡ ኤሊዛ፤ ይህ ዳጊ ይባላል። እሱ የመጣው ከጎንደር ነው። ዳጊ ጓደኛዬ ነው።
ዳጊ፣ ይቺ ኤሊዛ ትባላለች ። እሷ የመጣችው ከጀርመን ነው።

ዳጊ፡ ሰላም ኤሊዛ!

ኤሊዛ፡ ሰላም ዳጊ!

ፍጹም፡ ኤሊዛ አማርኛ ትችላለች።

ዳጊ፡ በውነት! ጎበዝ!!

ኤሊዛ፡ ሃሃሃ ትንሽ ትንሽ ብቻ!

ፍጹም፡ ዳጊ ፣ ተቀላቀለን፣ ሻይ ቡና በል!

ዳጊ፡ ደስ ይለኛል! ግን አሁን መሄድ አለብኝ። ፍጹም፣ ኤሊዛ; መልካም ቀን! ።!

ፍጹም፡ እሺ፤ ላንተም መልካም ቀን!

ኤሊዛ፡ እሺ፤ መልካም ቀን! ቻው ዳጊ!

አስተናጋጅ፡ እሺ፣ ይኸው፣ አንድ ቡና፣ አንድ ውሃና አንድ ቀዝቃዛ ኮካ ኮላ።

ፍጹም፡ እናመሰግናለን።

ኤሊዛ፡ አመሰግናለሁ።

አስተናጋጅ፡ ምንም አይደል!

## CD 7 - 11

## Activity 5

**CD 7 -** 1 የአሜሪካ ሙዚቃ
**CD 8 -** 2 የናይጄሪያ ሙዚቃ
**CD 9 -** 3 የቻይና ሙዚቃ
**CD 10 -** 4 የብራዚል ሙዚቃ
**CD 11 -** 5 የኢትዮጵያ ሙዚቃ

## CD 12

## Activity 7

ታድያስ ! ሰላም!

ጤና ይስጥልኝ!

ደህና አደርክ?
ደህና አደርሽ ?

ደህና አደሩ ?
ደህና አደራችሁ?

ደህና ዋልክ?
ደህና ዋልሽ?
ደህና ዋሉ?
ደህና ዋላችሁ?

ደህና አመሸህ
ደህና አመሸሽ
ደህና አመሹ
ደህና አመሻችሁ

መልካም ቀን!
መልካም ምሽት!
መልካም አዳር!

ደህና እደር!
ደህና እደሪ!
ደህና እደሩ!

ደህና ሁን!
ደህና ሁኚ!
ደህና ሁኑ!

## CD 13

## Activity 8

### ቃለ ምልልስ 1

ሮዛ፡ ታድያስ ሳሚ!

ሳሚ፡ ታድያስ ሮዛ

ሮዛ፡ እንዴት ነህ?

ሳሚ፡ በጣም ደህና ነኝ! አንቺስ እንደምን ነሽ?

ሮዛ፡ ደህና እግዜር ይመስገን! ክላስ እንዴት ነው?

ሳሚ፡ ክላስ አሪፍ ነው።

David joins

ሳሚ፡ ሄይ ዳቪድ! ሰላም ነው?

ዳቪድ ሰላም ናችሁ?

ሮዛ፡ ሰላም!

ሳሚ፡ ሮዛ፤ ይህ ዳቪድ ነው። ዳቪድ እንግሊዛዊ ነው። ዳቪድ እዚህ ዩኒቨርሲ exchange ተማሪ ነው። ዳቪድ፤ ይቺ ሮዛ ትባላቻ። ሮዛም እዚህ ተማሪ ናት።

ሮዛ፡ ወደ ካፌ እየሄድን ነው። ቡና መጠጣት ትፈልጋለህ?

ዳቪድ: ደስ ይለኛል።

## CD 14

### ቃለ ምልልስ 2

ዶ/ር ከበደ፡ ጤና ይስጥልኝ ወይዘሮ ጸሀይ!

ወ/ሮ ጸሀይ፡ አብሮ ይስጥልኝ፤ ዶክተር ከበደ!

ዶ/ር ከበደ፡ እንደምን ነዎት፤ ወይዘሮ ፀሀይ!

ወ/ሮ ጸሀይ፡ ደህና እግዜር የመስገን! እርሶስ እንደምን ነዎት?

ዶ/ር ከበደ፡ ደህና እግዜር ይመስገን!

ዶ/ር ከበደ፡ እንደምን አደሩ፤ ሚስተር ስሚዝ?

ሚ/ር ስሚዝ፡ እንደም ዶክተር ከበደ!

ዶ/ር ከበደ፡ ሚ/ር ስሚዝ ፤ እኚህ ወይዘሮ ፀሀይ ናቸው። ወ/ሮ ጸሀይ፤ እኚህ ሚስተር ስሚዝ ናቸው። ሚስተር ስሚዝ የመጡት ከአሜሪካ ነው። ሚስተር ስሚዝ አዲሱ የስራ ባልደርባችን ናቸው።

ሚ/ር ስሚዝ: ይቅርታ ስሞት ማን ነው?

ወ/ሮ ጸሀይ፡ ስሜ ፀሀይ ነው።

ሚ/ር ስሚዝ: ፀሀይ ፤ ወይዘሮ ጸሀይ!

ወ/ሮ ጸሀይ፡ መልካም። እንኳን ደህና መጡ ሚ.ር ስሚዝ።

ሚ/ር ስሚዝ: አመሰግንናለሁ።

# Chapter 2

## CD 15

### Activity 1a and 2a

ጋዜጠኛ ሰላም ናችሁ?
ስማችሁ ማን ነው?

ሄለን። ስሜ ሄለን ይባላል። ይህ ሄኖክ ነው። ሄኖክ ባለቤቴ ነው።

ጋዜጠኛ፡ ስንት ዓመታችሁ ነው?

ሄለን እኔ 28 ዓመቴ ነው።

ሄኖክ እኔ 33 ዓመቴ ነው።

ጋዜጠኛ፡ የት ኖርራላችሁ?

ሄኖክ አሁን አዲስ አበባ እንኖራለን።

ጋዜጠኛ፡ ልጅ አላችሁ

ሄለን: አዎ፣ ሁለት ልጅ አለን።

ሄኖክ: አንድ ሴት ልጅ እና አንድ ወንድ ልጅ።

## CD 16

### Activity 3a

1, 2, 3, 4, 5, 6, 7, 8, 9, 10, 11, 12, 13, 14, 15, 16, 17, 18, 19, 20, 21, 30, 40, 50, 60, 70, 80, 90, 100

## CD 17

### Activity 5a

ጋዜጠኛ: ስራችሁ ምንድን ነው?

ሄኖክ፡ እኔ መሀንዲስ ነኝ። ሚድሮክ ኢትዮጵያ እሰራለሁ።

ጋዜጠኛ: ሚድሮክ ኢትዮጵያ የግንባታ ድርጅት ነው፣ አይደል?

ሄኖክ፡ አዎ ልክ ነው።

ጋዜጠኛ: ሄለንስ፤ ስራሽ ምንድን ነው?

ሄለን፡ እኔ የሒሳብ ሰራተኛ ነኝ። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እሰራለሁ።

ጋዜጠኛ: ለቃለ ምልልሱ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ።

ሄለን: ምንም አይደል።

# Chapter 3

## CD 18

### Activity 1b

ጠይቂ: ማርታ፤ ይህ አባትሽ ነው?

ማርታ: አይ፣ ይህ አባቴ አይደለም። ይህ አጎቴ መኮንን ነው።

ጠይቂ: አሃ ነው እንዴ?! ይቺስ ማን ናት? እህትሽ ናት?

ማርታ: አዎ፣ ይቺ ታናሽ እህቴ ፀሀይ ናት።

ጠይቂ: ይህ ወንድምሽ ነው?

ማርታ: አዎ፣ ይህ ታላቅ ወንድሜ ቢኒያም ነው።

ጠይቂ: ይቺ እናትሽ ናት?

ማርታ: አዎ፣ ይቺ እናቴ ሜሮን ናት።

ጠይቂ: እነዚህ ማን ናቸው? አያቶችሽ ናቸው?

ማርታ: አዎ፤ እነዚህ አያቶቼ ናቸው።

## CD 19

### Activity 2b

ጠይቂ: ይህ አባትሽ ነው?

ማርታ: አይ፤ አይደለም። ይህ አጎቴ መኮንን ነው።

ጠይቂ: ይቺስ፤ ማን ናት? እህትሽ ናት?

ማርታ: አዎ፣ ይቺ እህቴ ፀሀይ ናት።

## CD 20

### Activity 2b

ወንድም - ወንድም እና እህት - እህት
አባት - ወላጆች - እናት
ወንድ አያት - አያቶች - ሴት አያት
ወንድ ልጅ - ልጆች - ሴት ልጅ
ወንድ የልጅ ልጅ - የልጅ ልጆች - ሴት የልጅ ልጅ

## CD 21

### Activity 5a

**a**

ጠያቂ፡ ያ አባትሽ ነው?

ሴት ፡ አይ፤ ያ አባቴ አይደለም። ያ አጎቴ ነው።

**b**

ጠያቂ፡ ያቺ እናትህ ናት፤ አይደል ?

ወንድ፡ አይ ያቺ እናቴ አይደለችም። አያቴ ናት።

**c**

ጠያቂ፡ እነዚያ ወላችጆሽ ናቸው?

ሴት: አዎ፤ ወላጆቼ ናቸው።

**CD 22-27**

**Activity 7a**

**CD 22**

1 እነዚህ ልጆቼ ናቸው። ስማቸው ዮሴፍና መኮንን ይባላል። ዮሴፍ ባለትዳር ነው። ሶስት ልጆች አሉት። ዮሴፍ ሃኪም ነው።።። መኮንን አስተማሪ ነው። መኮንን ባለትዳር አይደለም። አሁን ሃዋሳ ይኖራል.

**CD 23**

2 ባለቤቴ ሜሮን ትባላለች። 40 ዓመቷ ነው። የመጣችሁ ከኤርትራ ነው።

**CD 24**

3 ባለቤቴ ዮሴፍ ይባላል። ዮሴፍ 48 ዓመቱ ነው። ሃኪም ነው። እነዚህ ልጆቻችን ቢኒያም፣ ማርታ እና ፀሀይ ናቸው።

**CD 25**

4 ይህ ወንድሜ መኮንን ነው። እነዚህ አባት እና እናቴ ናቸው። አባቴ 79 ዓመቱ ነው። እናቴ 75 ዓመቷ ነው። ሁለቱም ጡረተኛ ናቸው።

**CD 26**

5 ይህ ታላቅ ወንድሜ ቢኒያም ነው። ይቺ ታናሽ እህቴ ፀሀይ ናት። ወንድሜ ቢኒያም 10 ዓመቱ ነው። አሁን የአራተኛ ክፍል ተማሪ ነው።

**CD 27**

6 እነዚህ እህቶቼ ማርታ እና ጸሀይ ናቸው። ማርታ 7 ዓመቷ ነው። ጸሀይ ደግሞ ገና 5 አመቷ ነው።

**CD 28**

**Activity 9a**

ይቺ እህቴ ሰላማዊ ናት። ሰላማዊት 33 ዓመቷ ነው። አሁን አዲስ አበባ ትኖራለች። ሰላማዊት tour guide ናት።

ሰላማዊት ብዙ ቋንቋ ትናገራለች። አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋዋ ነው። ከአማርኛ በተጨማሪ ኦሮምኛ ፣ እንሊዝኛ እና ፈረንሳይኛ በደንብ መናገር ትችላልች ትግርኛ ና ጀርመንኛ ደግሞ ትንሽ ትሞክራለች።

## Modul 1

**CD 29 -33**

**Activity ኢትዮጵያ ቋንቋዎች**

**CD 29 wänd**

አካም ጂርታ፣። ስሜ ገቢሴ ነው። 42 ዓመቴ ነው። የመጣሁት ከአንቦ ነው። አሁን አዲስ አበባ ቦሌ ቡልቡላ እኖራለሁ። ኦሮምኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ነው። አማርኛ እና እንግሊዝኝ በደንብ መናገር እችላለሁ። ሶማልኛ ደግሞ ትንሽ ትንሽ እችላለሁ። ባለትዳር ነኝ። ሁለት ልጅ አለኝ። ነጋቲ!

**CD 30 ሴት**

ትዕና ይሀበለይ። ስሜ አዜብ አብርሃ ይባላል። የመጣሁት ከትግራይ፤ አክሱም ከተማ ነው። 22 ዓመቴ ነው። አሁን ሃዋሳ ከተማ የዩኒቨርሲቲ እንጂነሪንግ ተማሪ ነኝ። ትግርኛ አማርኛና እንግሊዝኛ መናገር እችላለሁ። ደሃን ኩኑ!

**CD 31 ወንድ**

ኪሬሆ! ስሜ ገልፋቶ ነው። 42 ዓመቴ ነው። አሁን በሃዋሳ ከተማ እኖራለው። የቡና ነጋዴ ነኝ። ሲዳምኛ፣ አማርኛና ኦሮምኛ መናገር እችላለሁ። እንግሊዝኛ ትንሽ ትንሽ እናገራለሁ።

ባለትዳር ነኝ። ሶስት ልጆች አሉኝ። ካሀሪ!

**CD 32 ሴት**

ሰላም ቻላይኩም። ስሜ ፋጡማ ነው። እድሜዬ 28 ነው። ነርስ ነኝ። የመጣሁት ሶማሊያ ጅጅጋ ከተማ ነው። አሁን ድሬዳዋ እኖራለሁ። ሶማልኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ነው። እንሊዝኛና አማርኛ በደንብ መናገር እችላለሁ። ናባድ ጌሊ!

**CD 33 ወንድ**

ሰላም ጤና ይስጥልኝ! ስሜ መስፍን ነው። 25 አመቴ ነው። የመጣሁት ከጎንደር ከተማ ነው። አሁን ባህር ዳር እኖራለሁ። ባርዳር አንድ ትምህርት ቤት ውስጥ አስተማሪ ነኝ። አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ነው። እንግሊኛ መናገር እችላለሁ ፤ ትግርኛ ትንሽ ትንሽ እናገርለሁ። ሰላም ሁኑ!

## Chapter 4

### CD 34

### Activity 1

| | |
|---|---|
| ሄኖክ: | ሄለን እዚጋ እዪ! ወንበሩ በጣም ቆንጆ ነው። |
| ሄለን: | ቆንጆ ነው? ዋጋው ስንት ነው? |
| ሄኖክ: | እኔንጃ፣ አላውቅም። ህምምምም 8 500 ብር ነው። |
| ሄለን: | 8 500 ብር በጣም ውድ ነው። |
| ሄኖክ: | አይ፣ ውድ አይደለም። ጥሩ ዋጋ ነው። |
| ሄለን: | ኧረ በጣም ውድ ነው! |
| ሄኖክ: | ግን በጣም ቆንጆ ወንበር ነው። |
| ሄለን: | ቢሆንም! |

### CD 35

### Activity 3

| | |
|---|---|
| ሄለን፡ | እዚህ ጋ እዪ! ሶፋው በጣም ቆንጆ ነው! |
| ሄኖክ፡ | እኔም ወድጀዋለሁ! |
| ሄለን፡ | ይህ ሶፋ ዋጋው ስንት ነው? |
| ሻጭ፡ | እድለኛ ናችሁ አሁን ታላቅ ቅናሽ ላይ ነን! ሶፋው 10 500 ብር ብቻ! |
| ሄለን፡ | ርካሽ ነው። |
| ነጋዴ፡ | አዎ፣ ጥሩ ዋጋ ነው። |
| ሄለን፡ | ሶፋው በጣም ቆንጆ ነው! |
| ሄኖክ፡ | አዎ፣ ሶፋው ያምራል። |

### CD 36

### Activity 4b

here i need a a long with some beat!
ሶፋው፣ ጠረጴዛ፣ ቁም ሳጥኑ፣ ምንጣፉ፣ መደርደሪያው፣ አልጋው ፣ ወምበሩ፣ የራስጌ መብራቱ ፣ ፎቶው ፣ በርጩማው

### CD 37

### Activity 4b

1

| | |
|---|---|
| ሄለን፡ | እዚህ ጋር ተመልከት። ሶፋው በጣም ቆንጆ ነው። |
| ሄኖክ፡ | እኔም ወድጀዋለሁ። |

2

| | |
|---|---|
| ሄለን፡ | እዚጋ ተመልከቺ ። መብራቱ በጣም ያምራል። |
| ሄኖክ፡ | እኔም ወድጀዋለሁ። |

3

| | |
|---|---|
| ሄለን፡ | እዚህ ጋር ተመልከት። የግድግዳ ሰዓቱ በጣም ቆንጆ ነው። |
| ሄኖክ፡ | እኔ ግን አልወደድኩትም። |

### CD 38

### Activity 6

| | |
|---|---|
| 1 | 100፣ 200፣ 300 |
| 2 | 450፣ 451፣ 452 |
| 3 | 1 000፣ 10 000፣ 100 000 |
| 4 | 210 000 ፣ 320 000 ፣ 430 000 |

### CD 39-41

### Activity 6

### CD 39

a

| | |
|---|---|
| ሻጭ፡ | ሰላም! ምን ልርዳህ? |
| ደንበኛ፡ | ይህ ቁም ሳጥን ዋጋው ስንት ነው? |
| ሻጭ፡ | 14 500 ብር ነው። |
| ደንበኛ፡ | 14 500 ብር፣ ጥሩ ዋጋ ነው። |

### CD 40

b

| | |
|---|---|
| ደንበኛ፡ | ይቅርታ! |
| ሻጭ፡ | አቤት ምን ልርዳሽ? |
| ደንበኛ፡ | የራስጌው መብራት፤ ዋጋው ስንት ነው? |
| ሻጭ፡ | መብራቱ 9 800 ብር ነው። |
| ደንበኛ፡ | 9 800 ብር ! ? በጣም ውድ ነው! |
| ሻጭ፡ | የጣልያን ነው። ጥሩ እቃ ነው። |

### CD 41

c

| | |
|---|---|
| ደንበኛ፡ | ይቅርታ! |
| ሻጭ፡ | አቤት ምን ልርዳዎት? |
| ደንበኛ፡ | ይህ ሶፋ ዋጋው ስንት ነው? |
| ሻጭ፡ | 92 000 ብር ብቻ ነው። |
| ደንበኛ፡ | 92 000 ብር? በጣም ውድ ነው! |
| ሻጭ፡ | አዎ፣ ዲዛይነር ሶፋ ነው! |
| ደንበኛ፡ | 92 000 ብር ? .... |

**Activity 6**

**CD 42**

ሴት፡ ክፍሉ በጣም ያምራል። አልጋው ዘመናዊ ነው።

ወንድ፡ አው፣ ክፍሉ በጣም ቆንጆና ዘመናዊ ነው። ቁም ሳጥኑን ግን አልወደድኩትም። በጣም ትንሽ ነው።

ሴት፡ አዎ፣ ልክ ነህ። ቁም ሳጥኑ ትንሽ ነው።

## Chapter 5

**CD 43**

**Activity 1**

ኤደን፡ ተመልከት አባ!

አባ፡ ዎው፣ በጣም ቆንጆ ነው። ይህ ምንድን ነው? ጠረጴዝ ነው?

ኤደን፡ ጠረጴዛ? አይ፣ ይህ ጠረጴዛ አይደለም።

አባ፡ ጠረጴዛ አይደለም...? ሰዓት ነው?

ኤደን፡ አይ፤ ሰዓትም አይደለም።

አባ፡ እሺ ታድያ ምንድን ነው?

ኤደን፡ አሁንስ?

አባ፡ አሃ፤ አንዴ ቆይ! አሁን ምን እንደሆነ አውቃለሁ። ስልክ ነው?

ኤደን፡ ሃሃሃ ፤ ስልክ አይደልም።

አባ፡ ስልክ አይደለም። ታድያ ምንድን ነው?

ኤደን፡ መኪና ነው።

አባ፡ አሃ ነው እንዴ? አዎ፣ አሁን ይታየኛል። መኪና እሺ አሁን ደግሞ የኔ ተራ ነው። ይህ ምንድን ነው?

**CD 44**

**Activity 1**

a

ኤደን፡ ይህ መጽሐፍ ነው?

አባ፡ አይ፤ ይህ መጽሐፍ አይደለም።

b

ኤደን፡ ይህ ጠረጴዛ ነው?

አባ፡ አይ፣ ይህ ጠረጴዛ አይደለም።

c

ኤደን፡ ይህ ወንበር ነው?

አባ፡ አዎ ልክ ፣ ይህ ወምበር ነው።

**CD 45 - 48**

**Activity 5a**

**CD 45**

a

ሴትዮ፡ አመሰግናለሁ።

ሰዉዬ፡ ምንም አይደል።

ሰውዬ፡ ይህ በአማርኛ ምን ይባላል? ላይተር?

ሴትዮ፡ አዎ፣ ልክ ነው። ይህ በአማርኛ ላይተር ይባላል።

ሰውዬ፡ እሺ።

ሴትዮ፡ አመሰግናለሁ።

ሰውዬ፡ ምንም አይደል።

**CD 46**

b

ሰውዬ፡ ይቅርታ ይህ በአማርኛ ምን ይባላል?

ሴትዮ፡ ይህ ብር ነዋ!

ሰውዬ፡ አይ እሱን አይደለም። ይህን ነው። ዋሌት በአማርኛ ምን ይባላል?

ሴትዮ፡ ነው እንዴ፤ የኪስ ቦርሳ።

ሰውዬ፡ ይቅርታ ምን አልሽኝ?

ሴትዮ፡ የኪስ ቦርሳ!

ሰውዬ፡ የኪስ ቦርሳ። እሺ አመሰግናለሁ።

**CD 47**

c

ሰውዬ፡ ይቅርታ! [ሰውዬው ያስነጥዛል]

ሴትዮ፡ ይማርህ!

ሰውዬ፡ ያኑርሽ። ናብኪን ትፈልጊያለሽ?

ሴትዮ፡ ደስ ይለኛል። አመሰግናለሁ።

ሰውዬ፡ ይህ በአማርኛ ናብኪን ይባላል?

ሴትዮ፡ አዎ፣ ልክ ነው። ይህ በአማርኛ ናብኪን ይባላል።

ሰውዬ፡ እሺ። አመሰግናለሁ።

**CD 47**

d

ሴትዮ፡ 1 መጠለል ትፈልጋለህ?

ሰውዬ፡ 2 በጣም አመሰግናለሁ። umbrella በአማርኛ ምን ይባላል?

ሴትዮ፡ 1 umbrella በአማርኛ ዣንጥላ ወይም ጥላ ይባላል።

ሰውዬ፡ 2 ይቅርታ ምን አልሽኝ?

ሴትዮ፡ 1 ዣንጥላ፣ ዣንጥላ።

ሰውዬ፡ 2 ዣንጥላ...ዣንጥላ... እሺ አመሰግናለሁ።

ሴትዮ፡ 1 ምንም አይደል።

## Chapter 6

### CD 49-52

### Activity 1a

### CD 49

a

ዛሬ ኢንተርኔት የለም እንዴ? ምን!? የይለፍ ቃሉ ልክ አይደም። ፓስዎርዱ አዲስ ነው እንዴ?
ምን አይነት ነገር ነው?
አሃ። አው! አሁን ሰራ ...

### CD 50

b

ምን? ፕሪንተሩ አይሰራም ወይስ ቀለም የለውም። out of toner ... እጭ አስቸኳይ ነበር። አሁን ምን ይሻላል። ዮሃንስ የት ነው? ምን አይነት ነገር ነው?!

### CD 51

c

ሰውዬ: ካላንደሩ የት ነው? ወይዘሮ ጸሀይ፤ ካላንደሩ የት ነው? ወይዘሮ ጸሀይ ካላንደሩ እርሶ ጋር ነው።

ሴትዮ፡ አይ እኔ ጋር አይደለም።

ሰውዬ: ይሀ፣ ካላንደሩ ይኸውና። እሺ ታብሌቱስ፣ አንቺ ጋር ነው?

ሴትዮ አይ, እኔጋር አይደለም, ታብሌቱ ዮሀንስ ጋር ነው። ዛሬው ስራ ደግሞ ልዩ ነው! ብዙ ስራ። ለምሳ ጊዜ ጠፋ!
በርገሬ ቀዘቀዘ!

### Activity 4

### CD 52

መቅደስ: ሄሎ ዮሃንስ! መቅደስ ነኝ።

ዮሃንስ: ሄሎ መቅደስ! ምን ልርዳሽ?

መቅደስ: ፕሪንት ማድረግ ፈልጌ ነበር። ነገር ግን ፕሪንተሩ ቀለም የለውም። አስቸኳይ ነበር።

ዮሃንስ: እሺ። አዲስ ቀለም አሁን እቀይራለሁ። ከ15 ደቂቃ በኋላ ፕሪንት ማድረግ ትችያለሽ

መቅደስ: እሺ! በጣም አመሰግናለሁ።

ዮሃንስ: ምንም አይደል።

### Activity 4

### CD 53

ሰውዬ: ካላንደሩ የት ነው? ወይዘሮ ፀሀይ ካላንደሩ እርሶ ጋር ነው?

ፀሀይ፡ አይ፤ እኔ ጋር አይደለም።

ሰውዬ: አሀ፣ ካላንደሩ እዚህ ነው። እሺ ታብሌቱስ የት ነው? ታብለቱ እርሶ ጋር ነው?

ፀሀይ፡ ታብሌቱ ዮሃንስ ጋር ነው።

### Activity 9

### CD 54

ፀሀይ: ሰላም ጤና ይስጥልኝ ፣ ሚድሮክ ኢትዮጵያ ። ጸሀይ ማሞ ነኝ። ምን ልርዳዎት?

ስልክ: አብሮ ይስጥልኝ። አቶ ከበደን ማናገር ፈልጌ ነበር። አቶ ከበደ አሉ?

ፀሀይ: አንዴ መስመር ላይ ይቆዩ። .... አቶ ከበደ ዛሬ ቢሮ የሉም።

ፀሀይ: እሺ አመሰግናለሁ።

ስልክ: ስለደወሉ እናመሰግናለን።

## Modul 2

### Page 40

### ምን ያስፈልጋልችኋል? ምን አያስፈልጋችሁም?

### CD 55

a

ሜሮን: እምምምም እኔ ምን ያስፈልገኛል? ህምምምም ምን አያስፈልገኝም። ጠረጴዛ አያስፈልገኝም። ሃሃሃሃ ...

### CD 56

b

ፊሊሞን: እኔ ወንበር አያሰፈልገኝም።

### CD 57

c

ሃብቶም: አዎ፣ ዛሬ ወደ ፓርክ እንዳሄዳለን። ጠረጴዛም ወንበርም አያስፈልገግንም።

### CD 58

d

ሜላት፣
ኤልሳ፣
ኤደን። ኮምፒተር አያስፈልገንም።

### Activity 1a

### CD 59 song ጤና ይስጥልኝ!

## Chapter 7

### CD 60

### Activity 1a

a

ወንድ፡ ዎው! በደንብ መደነሽ ትችያለሽ!

ሴት፡ ምን?

ወንድ፡ በደንብ መደነስ ትችያለሽ!

ሴት፡ ምን? አይሰማኝም።

ወንድ፡ በደንብ መደነስ ትችያለሽ! ዳንስ ጎበዝ ነሽ!!!

ሴት፡ ኦ፣ አመሰግናለሁ።

ወንድ፡ ስምሽ ማን ነው?

ሴት፡ ምን?

b

ሳሚ፡ የአይኖችሽ ከለር ምንድን ነው?

ርብቃ፡ የአይኖቼ ከለር ምንድን ነው ሳሚ?

ሳሚ፡ አንዴ ቆይ, ጥቁር፣ አረንጓዴ፣ ቡኒ .....

ርብቃ፡ ትንሽ ግራጫስ ...?

ሳሚ፡ ግራጫ? እኔንጃ አላውቅም። አይኖችሽ በጣም ቆንጆ ናቸው።

ርብቃ፡ኦህ፣ አንዴ ትደግመው?

ሳሚ፡ ርብቃ እጅግ በጣም ቆንጆ ነሽ!

።:)

c

ሳሚ፡ ህምምምም

ርብቃ፡ ሳሚ!!

ሳሚ፡ ህምምምም

ርብቃ፡ ሳሚ..

ሳሚ፡ ዋው! በጣም ይጣፍጣል!

ርብቃ፡ ሳሚ!

ሳሚ፡ ርብቃ። በጣም ይጣፍጣል!

ርብቃ፡ በውነት?

ሳሚ፡ በውነት! በደንብ ማብሰል ትችያለሽ!

ርብቃ፡ በውነት! አመሰግናለሁ!! ሳሚ!!!!

### CD 61-63

### Activity 9a and b

**CD 61** 1

ፍጹም: ሰላም! ስሜ ፍጹም ይባላል። በትርፍ ጊዜዬ እግር ኳስ መጫወት እወዳለሁ። እነዚህ ጓደኞቼ ናቸው። ሁላችንም በደንብ ኳስ መጫወት እንችላለን። በሳምንት አንድ ጊዜ እዚህ ፓርክ ውስጥ እንጫወታለን። እግር ኳስ መጫወት ያዝናናኛል። ሁላችንም እግር ኳስ በጣም እንወዳለን።

ጓደኛ: ፍፁም ቶሎ ና እንጂ። ልንጀምር ነው።

ፍጹም: እሺ መጣው መጣው!

**CD 62** 2

ስሜ ሂዎት ይባላል። የሙዚቃ አስተማሪ ነኝ። ሙዚቃ ማዳመጥ በጣም እወዳለሁ። ጊታር፣ ፒያኖና ክራር መጫወት እችላለሁ። ጃዝ ሙዚቃ መስማት እወዳለሁ። የሙላቱ አስታጥቄዎችን ሙዚቃ በብዛት አዳምጣለሁ። በትርፍ ጊዜዬ ፊልም ማየት እወዳለሁ። አልፎ አልፎ ሲኒማ ቤት ከጓደኞቼ ጋር እሄዳለሁ።

**CD 63** 3

ስሜ ሚሪያም ይባላል። የመጣሁት ከጀርመን ሀገር ነው። አሁን አዲስ አበባ እኖራለሁ። አማርኛ በደንብ መናገር እችላለሁ። በትርፍ ጊዜዬ ፈረስ መጋለብ፣ የእግር ጉዞ ማድረግና ብስክሌት መንዳት እወዳለሁ። ተፈጥሮ በጣም እወዳለሁ።

## Chapter 8

### CD 64

### Activity 1

አስተናጋጅ፡ አንድ ማኪያቶ!

ሳባ፡ አመሰግናለሁ።

አስተናጋጅ፡ ምንም አይደል።

ሳባ ከሙሴ ጋር ሃሎ አቤል! ዛሬ ከሰዓት? ገና አላውቅም። ትያትር ቤት እንሂድ? ... ትያትር ቤት መሄድ አልፈልግም። ሲኒማ ቤት ? ስንት ሰዓት ? አስር ሰዓት? እሺ። ቻው።

ሳባ ከአቤል ጋር ሰላም ሰላም ሙሴ! ጠፋህ! እንዴትን ነህ። እኔ ደህና ነኝ። ... ምን እያደረክ ነው። ሲኒማ ቤት ? በጣም ደስ ይለኛል። ጥሩ ሃሳብ ነው። ስንት ሰዓት? ዛሬ ከሰዓት ? አስር ሰዓት? ኧረ ችግር የለም። ጊዜ አለኝ። እሺ ። በኋላ እንገናኝ። ቻው።

### CD 65

**Activity 3a**

ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ እሮብ/ረቡዕ፣ ሃሙስ፣ አርብ፣ ቅዳሜ፣ እሁድ/ሰንበት

### CD 66

**Activity 3a**

ጠዋት፣ ረፋድ፣ ቀትር፣ ከሰአት፣ ማታ፣ ለሊት

### CD 67

**Activity 3a**

1 - ስንት ሰዓት ነው? ሶስት ሰዓት ከአስር
2 - ስንት ሰዓት ነው? ዘጠኝ ሰዓት ከአምስት።
3 - ስንት ሰዓት ነው? አስር ሰዓት ከሩብ ።
4 - ስንት ሰዓት ነው? አስራ ሁለት ሰዓት ከሀያ።
5 - ስንት ሰዓት ነው? ስድስት ከሃያ አምስት
6 - ስንት ሰዓት ነው?ስምንት ሰዓት ተኩል
7 - ስንት ሰዓት ነው?
ለሁለት ሰዓት ሃያ አምስት ጉዳይ።
8 ስንት ሰዓት ነው? ለስምንት ሃያ ጉዳይ።
9 - ስንት ሰዓት ነው? ለስድስት ሰዓት ሩብ ጉዳይ።

## Chapter 9

### CD 68

**Activity 3**

ሰውዬ፡ ቁርስ ምን መብላት ትወዳለህ?
ሴትዮ፡ እንቁላል ፍርፍር መብላት እወዳለሁ። አንቺስ ቁርስ ምን መብላት ትወጃለሽ?
ሰውዬ፡ ብዙ ጊዜ ቁርስ አልበላም። ቡና ብቻ እጠጣለሁ። ቁርስ በስንት በስንት ሰዓት ትበላለህ?
ሴትዮ፡ ከሰኞ እስከአርብ ጠዋት 1 ሰዓት፣ ቅዳሜና እሁድ ግን 5 ሰዓት አካባቢ እበላለሁ

### CD 69

**Activity 5**

ዳቪድ፡ አበባ!
ሜላት፡ በጣም አመሰግናለሁ።
ዳቪድ፡ ምንድን ነው?
ሜላት፡ ዶሮ ወጥ ነው። ዶሮ ወጥ ታውቃለህ?
ዳቪድ፡ እኔንጃ አላውቅም።
ሜላት፡ መልካም ምግብ!
ዳቪድ፡ ለሁላችን
ሜላት፡ ብላ እንጂ!
ዳቪድ፡ በቃኝ! ጠገብኩ! ሶፍት አለ?
ሜላት፡ ቡና ትፈልጋለህ?
ዳቪድ፡ ደስ ይለኛል?
ሜላት፡ ቡና በሃበሻ ወይስ በፈረንጅ አረቄ?
ዳቪድ፡ ሽንት ቤት የት ነው?

### CD 70

**Activity 6a**

አስተናጋጅ ሰላም ናችሁ? የሚጠጣ ምን ልታዘዝ?
አባት፡ ለኔ አንድ ሀበሽ ቢራ።
አስተናጋጅ፡ ይቅርታ። እዚህ አልኮል መጠጥ የለም።
አባት፡ እሺ፤ ለኔ አንድ ቡና።
አስተናጋጅ፡ የጀበና ወይስ የማሽን ቡና?
አባት፡ የጀበና ቡና።
እናት፡ ለኔም አንድ የጀበና ቡና እና አንድ ሊትር ውሃ።
አስተናጋጅ፡ ቀዝቃዛ ወይስ ከውጭ ይሁን?
እናት፡ ቀዝቃዛ ይሁን።
አባት፡ ልጆች የሚጠጣ ምን ትፈልጋላችሁ?
ናቲ፡ ለኔ አንድ ኮካ ኮላ።
አባት፡ ላንቺስ ኤደን?
ኤደን፡ ለኔ አንድ ሚሪንዳ።
አስተናጋጅ፡ የሚበላስ ትፈልጋላችሁ?
አባት፡ ለኔ አንድ ሰላጣ።
እናት፡ ለኔ አንድ የቲማቲም ሾርባ።
አባት፡ እሺ። ልጆች ለናንተስ?
ናቲ፡ ለኔ አንድ ሙዝ ኬክ ።
አባት፡ ላንቺስ፤ ኤደን። የሚበላ ምን ትፈልጊያለሽ?
ሄኖክ፡ አንድ ቺፕስ።
አስተናጋጅ፡ ሌላስ?
አባት፡ በቃ። እናመሰግናለን።

# Modul 3

### ቁርስ

### CD 71 ሄኖክ

ታድያስ! ስሜ ሄኖክ ይባላል። ቁርስ? አይ አመሰግናለሁ። ይቅርብኝ። ጠዋጥ ጠዋት ከነጭራሹ መብላት አልችልም። አይበላልኝም። ቡና ብቻ እጠጣለሁ። ብዙ ቡና እጠጣለሁ። ሁለት ሶስት ሲኒ ቡና።

### CD 72 ሳራ

ሰላም! ስሜ ሳራ ይባላል። ቁርስ መብላት በጣም እወዳለሁ። ብዙ ጊዜ ቅዳሜና እሁድ ከጓደኞቼ ጋር እገናኛለሁ፣ አንድ ላይ ቁርስ እንበላለን። እንቁላል ፍርፍር፣ ጨጨብሳ፣ ፉል፣ እርጎ፣ ማር ፣ ፍራፍሬ ፣ ጁስ። ሻይ ቡና ምናንም። ከሰኞ እስከ አርብ ጊዜ የለኝም። ስለዚህ ኮርን ፍሌክስ እና ፍረፍሬ ለቁርስ እበላለሁ።

### CD 73 ኤደን

ሰላም ናችሁ! ስሜ ኤደን ይባላል። እኔ ዳቦ አልወድም። ብዙ ጊዜ ለቁርስ አበስላለሁ። ብዙ ጊዜ ጠዋት ጠዋት እንቁላል ፍርፍር እሰራለሁ። አንዳንዴ ደግሞ ገንፎ ፣ ወይም ፍርፍር ወይም ዱለት። ዛሬ ቁርስ እንቁላል ፍርፍር ነው።

## Chapter 10

### CD 74

### Activity 2, 3, 4

| | |
|---|---|
| ሳራ | ሃሎ ሳራ፣ የኔ ውድ! |
| ማርቆስ | ሃሎ ማርቆስ ማሬ! እንደምን ነሽ? አሁን የት ነሽ? |
| ሳራ | አሁን ፍራንክፈርት ኤርፖርት ነኝ። በረራዬ የማታ ነው። |
| ማርቆስ | በረራሽ ስንት ሰዓት ነው። |
| ሳራ | ወደ ኢስታንቡል ማታ 1:30 ነው። |
| ማርቆስ | ኢስታንቡል ስንት ሰዓት ትደርሻለሽ? |
| ሳራ | ኢስታንቡል ማታ 4:30 እደርሳለሁ። |
| ማርቆስ | ከኢስታንቡል ወደ አዲስ አበባ በረራሽ ስንት ሰዓት? |
| ሳራ | ከኢስታንቡል ወደ አዲስ አበባ በረራው ለሌት 6:30 ነው። አዲስ አበባ ጠዋት 1:00 እደርሳለሁ። |
| ማርቆስ | ኢስታንቡል ስትደርሺ ትደውይልኛልሽ? |
| ሳራ | እንዴ በለሊት! እርግጠኛ ነህ? |
| ማርቆስ | አዎ እርግጠኛ ነኝ። ድምጽሽን መስማት እፈልጋለሁ። |
| ሳራ | እሺ እሞክራለሁ። እወድሃለሁ የኔ ፍቅር! |
| ማርቆስ | እኔም እወድሻለሁ የኔ ማር! መልካም በረራ! |
| ሳራ | አመሰግናለሁ። ደህና እደር! |

### CD 75

### Activity 6

| | |
|---|---|
| ማርቆስ፡ | ሰላም ማሬ እንደምን አደርሽ? |
| ሳራ፡ | ሰላም ውዴ! እንደምን አደርክ? |
| ማርቆስ፡ | አሁን በሌ አየር ማረፊያ የመኪና ማቆሚያ ቦታ ነኝ! |
| ሳራ፡ | እሺ፤ ጥሩ! አሁን ሻንጣ እየጠበኩ ነው።። |
| ማርቆስ፡ | ከስንት ደቂቃ በኋላ ትወጫለሽ? |
| ሳራ፡ | እኔንጃ፣ ገና አላወኩም። ምናልባት ከ 20 ደቂቃ በኋላ እወጣለሁ። |
| ማርቆስ፡ | እሺ። ልክ ልትወጪ ስትይ ትደውይልኛልሽ? |
| ሳራ፡ | እሺ። እደውልልሃለሁ። |
| ማርቆስ፡ | መውጫው ጋር እጠብቅሻለሁ። |
| ሳራ፡ | እሺ። |

### CD 76

### Activity 7

| | |
|---|---|
| ደንበኛ፡ | ሰላም፤ ጤና ይስጥልኝ! |
| ትኬት ቆራጭ፡ | አብሮ ይስጥልኝ! |
| ደንበኛ፡ | የባቡር ትኬት ፈልጌ ነበር! |
| ትኬት ቆራጭ፡ | ወዴት? |
| ደንበኛ፡ | ወደ ጅቡቲ። |
| ትኬት ቆራጭ፡ | ደርሶ መልስ ነው ወይስ መሄጃ ብቻ? |
| ደንበኛ፡ | መሄጃ ብቻ። |
| ትኬት ቆራጭ፡ | ለመቼ ነው? |
| ደንበኛ፡ | ለሚመጣው አርብ። |
| ትኬት ቆራጭ፡ | እሺ። ለስንት ሰው ነው? |
| ደንበኛ፡ | ለአራት ሰው ነው። |
| ትኬት ቆራጭ፡ | እሺ። የውጭ ሀገር ዜጋ ወይስ ኢትዮጵያዊ? |
| ደንበኛ፡ | ሁለት ኢትዮጵያዊ እና ሁለት የውጭ ሀገር ዜጋ። |
| ትኬት ቆራጭ፡ | እሺ። ፓስፖርት ያስፈልጋል። |
| ደንበኛ፡ | እሺ። ይኸው። |
| ትኬት ቆራጭ፡ | እሺ። 4 ትኬት 3500 ብር። |
| ደንበኛ፡ | እሺ። ይከው። |
| ትኬት ቆራጭ፡ | 4 ትኬት መልስ 100 ብር። |
| ደንበኛ፡ | ባቡሩ ከአዲስ አበባ ስንት ሰዓት ይነሳል? |
| ትኬት ቆራጭ፡ | ባቡሩ ከአዲስ አበባ ጀሞ ባቡር ጣብያ አርብ ጠዋት 12 ሰዓት ይነሳል። |
| ደንበኛ፡ | እሺ። አመሰግናለሁ። መልካም ቀን! |

**CD 77**

**Activity 8a**

ደንበኛ፡ ሰላም ነው?
ሹፌር፡ ሰላም ነው።
ደንበኛ፡ ታክሲ ፈልጌ ነበር።
ሹፌር፡ ወዴት ነዎት?
ደንበኛ፡ ወደ ቦሌ ኤርፖርት።
ሹፌር፡ አሁን የት ነዎት?
ደንበኛ፡ አሁን ራዲሰን ብሉ ሆቴል ነኝ።
ሹፌር፡ እሺ። መጣሁ። ከሁለት ደቂቃ በኋላ እደርሳለሁ።
ደንበኛ፡ እሺ። አመሰግናለሁ።

## Chapter 11

**CD 78 - 83**

**Activity 1 and 2**

**CD 78**

a

ሰላም ስሜ ኤልሳቤት ነው። ይህ ውሻዬ ሚኪ ነው። ትላንትና ጠዋት ከውሻዬ ሚኪ ጋር ወደ ጫካ ሄድኩ፣ ከውሻዬ ጋር ተጫወትኩ። ጫካ ውስጥ ሌሎች ውሻዎች ነበሩ። ሚኪ ከውሾቹ ጋር ተጫወተ።

**CD 79**

b

ትላንትና ምን አደረኩ። ትላንትና ቀኑን ሙሉ ያለ እረፍት ስራ ሰራሁ። አሁን በጣም ደክሞኛል ስለዚህ ከስራ በኋላ ቀጥታ ወደ ቤት ባለቤቴ ና ልጆቼ ጋር እሄዳለሁ። ቻው። መልካም ምሽት!

**CD 80**

c

ትላንትና እስከ 6:30 ሰራሁ። ከሰዓት ወደ ሱፐርማርኬት ሄድኩና አስቤዛ አደረኩ። ሌላ ምን አደረኩ? እራት ፓስታ ሰራሁ፣እቃ አጠብኩና እግር ኳስ ጨዋታ አየሁ።

**CD 81**

d

ትላንትና ምን አደረኩ። ትላንትና ቀኑን ሙሉ ለፍተና ተዘጋጀሁ። ምግብ ለመብላት እንኳን ጊዜ አለነበረኝ። 6 ሲኒ ቡና ጠጣሁ። የዩኒቨርሲቲ final exam፣ ከአንድ ሳምትን በኋላ ነው። ስለዚህ ተጨናንቂያለሁ። ቴንሽን ይዞኛል።

**CD 82**

e

ትላንትና እረፍት ነበረኝ። ቤቴ በጣም ቆሽሾ ነበር። ስለዘህ ቤቴን ቀኑም ሙሉ አፀዳሁ። ምሳ ሰራሁ ና ከጓደኛዬ ጋር ምሳ በላሁ።

**CD 83**

f

ትላንትና ምን አደረኩ?እምምምም፣ ትላንት ብዙ ነገር አላደረኩም። ጠዋት ከ3 ሰዓት እስከ 5 ሰዓት ጋዜጣ አነበብኩ፣ ከሰዓት ትንሽ ስፖርት ሰራርሁና ለአንድ ሰዓት ከልጄ ጋር በስልክ አወራሁ። ማታ ጓደኞቼን አገኘሁ።

## Chapter 12

**CD 84**

**Activity 1 and 2**

ያለፈው ዓመት የካቲት ወር የት ነበርኩ። አዲስ አበባ፣ ስዊዘላንድ .. እምምም አንዴ ቆይ ፣ አሁን አስታወስኩ። ያለፈው ዓመት የካቲት ወር ከጓደኞቼ ወደ ሃዋሳ ሄድኩ። በሃዋሳ ከተማ የግማሽ ማራቶ ሩጫ ውድድር ላይ ተሳተፍኩ።
የሃዋሳ 8 ኪሎ ሜትር እና ግማሽ ማራቶን ሩጫ ውድድር ከ2002 ጀምሮ በየዓመቱ የካቲት ወር እሁድ ቀን ይደረጋል።

ሩጫ መሮጥ በጣም እወዳለሁ። ነገር ግን ቀደም ብሎ ግማሽ ማራቶን ሩጫ ሮጬ አላውቅም ነበር። ስለዚህ ትንሽ ፈርቼ ነበር። ነገር ግን ሩጫው ጥሩ ነበር። እኔ ከአማተር አንደኛ ወጣሁ። የገባሁበት ሰዓት 1 ሰዓት ከ39 ደቂቃ ነበር። ከሩጫ ውድድሩ በኋላ ወደ ሀይሌ ሪዞርት ሄደንና ዋና ዋኘን፣ እራት በላን፣ ማሳጅ ተደረግን፤ ተዝናናን።

**CD 85**

**Activity 6a**

ጠያቂ፡ እረፍት እንዴት ነበር?
ሊያ፡ በጣም ቆንጆ ነበር። ያለፈው ታህሳስ ወደ ባህር ዳር ሄድኩ።
ጠያቂ፡ እንዴት ነበር።
ሊያ፡ በጣም ቆንጆ ነበር።
ጠያቂ፡ ስንት ቀን ቆየሽ?
ሊያ፡ አጠቃላይ አራት ቀን ቆየሁ።
ጠያቂ፡ ምን አደረግሽ?
ሊያ፡ ጣና ሀይቅን እና ቤተክርስትያኑን ጎበኘን። ወደ አባይ ፏፏቴ በመኪና ሄደን የአባይ ፏፏቴን አየን።
በባህርዳ ከተማ የባህል ሙዚቃና ጭፈራ አየን። ብዙ አሳ በላን።
ጠያቂ፡ ብስክሌት ነዳቹ?
ሊያ፡ አዎ፣ ከሆቴላችን ተነስተን እስከ የቀድሞ ቤተ መንግስት በሳይክል ሄደን ጎበኘን። በጣም ቆንጆ ጊዜ በባህር ዳር አሳልፈን።